

# ከኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ በወቅታዊ የሀገራችን ጉዳይ ላይ የተሰጠ መግለጫ

እንደሚታወቀው ዘረኛው የወያኔ ቡድን ገና ከምስረታው ጀምሮ የአማራን ህዝብ እንደ ህዝብ በጨቋኝነት በመፈረጅና በጠላትነት በማስቀመጥ ጊዜው አመቺ ሆኖ ሲያገኘውም የተለያዩ የጅምላ ጭፍጨፋዎችን ሲያካሂድበት ኖሯል።

ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የጥቃት አድማሱን በማስፋት በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ የአማራ ብሔር ተወላጆችን ቤትና ንብረታቸውን እየተዘረፉ እንዲባረሩ እያደረገ ይገኛል።ይኸውም ባለፈው አመት ከጉራፈርዳ 78,000 (ሰባ ስምንት ሺህ) ሰዎች እንዲፈናቀሉ ሲደረግ በዘንድሮ አመትም ከቤኒሻንጉል፣ከአፋር፣ከጅጅጋና ከቤንች ማጂ ዞኖች በርካቶች ቤት ንብረታቸው ተወርሶ የአማራ ብሔር ተወላጅ በመሆናቸው ብቻ እንዲፈናቀሉ እየተደረገ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ዘብም በሀገራችን እየተፈፀመ ያለውን የዘር ማፅዳት ወንጀል አጥብቆ የሚያወግዝ ከመሆኑ ባሻገር በዚህ አስከፊ ወንጀል ላይ ከወያኔ ጋር በመሆን በድርጊቱ ተባባሪ የሆኑ አካላት ጭምር በአለም አቀፉ የፍርድ ችሎት ሊቀጡ ይገባል የሚል ፅኑ አቋም አለን።በዚህ አጋጣሚ በሀገር ውስጥ ለአለም አቀፉ ፍርድ ቤት በማስረጃነት ይረዳ ዘንድ መረጃ እያሰባሰቡ ላሉት ፍትህ ወዳድ ኢትዮጵያውያን ያለንን አክብሮት ከመግለፅ ጎን ለጎን አስፈላጊውን የማቴሪያል፣የገንዘብና የሰው ኃይል እገዛ ለማድረግ ያለንን ቁርጠኝነት ለመግለፅ እንወዳለን።

በሌላ በኩል የዚህ አይነቱ የዘር ማፅዳት ወንጀል በሩዋንዳ እንደታየው በሂደት መልኩን እየቀየረ ከፍተኛ የሆነ ደም መፋሰስን ሊያስከትል ወደሚችል እልቂት ሊያመራ እንደሚችል ይገመታል። በመሆኑም የዚህ ዘረኛ ፖሊሲ አራማጅ የሆነውን የወያኔ መንግስት ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ውስጥ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ጉልህ

አስተዋፅኦ ለማድረግ ጊዜው አሁን ነው የሚል ፅኑ እምነት አለን። ይህም ሀገራችን ከቆመችበት መስቀለኛ መንገድ አንፃር የሚደረገው ፀረ-ወያኔ ትግል የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ በመሆኑ ሁሉም ዜጋ ለነፃነቱ፣ ለሀገራችን ህልውና ብሎም ከተደቀነብን ደም አፋሳሽ እልቂት ህዝባችንን ለመጠበቅ በአንድነት ይነሳ!!!

**ሁሉም ለእናት ሀገሩ ዘብ ይቁም!!!**

**የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ**

**ኤፕሪል 10, 2013**